# የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች የዓለም ጸረ ኤድስ ቀንና የነጭ ሪቫን ቀንን አከበሩ

"አንድም ሰው በኤች አይ ቪ እንዳይያዝ ኃላፊነታችንን በመወጣት የሀገራችንን ኀዳሴ እናሳካለን!" በሚል መሪ ቃል በዓለም ለ25ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ24ኛ ጊዜ የተከበረው የዓለም ጸረ ኤድስ ቀን እንዲሁም በአገራችን ለ8ኛ ጊዜ የተከበረው የነጭ ሪቫን ቀን የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሠራተኞች በተገኙበት ኅዳር 26 ቀን 2006 ዓ.ም ከቀኑ 8:00 - 11:00 ተከብሯል፡፡



አቶ ወንድሙ ኩመራ የኢንስቲትዩቱ የሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ባደረጉት መክፈቻ ንግግር ሰራተኞች ከHIV/AIDS ራሳቸውን እንዲጠብቁና ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች አስፈላጊውን ድጋፍና ክብካቤ ማድረግ እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

አያይዘውም ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ ሙሉ ግንዛቤ ከማግኘት እንዳይዘናጉና ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን የኢንስቲትዩቱን ዋና ዳይሬክተርን በመወከል መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡



ከአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ባለሙያ በሆኑት በአቶ አበባየሁ ይገረሙ ስለኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ ትምህርት የተሰጠ ሲሆን በሠራተኞች ውይይት ተደርጓል፡፡

አቶ አበባየሁ እንዳብራሩት ከሆነ አገራችን ስለኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከል በኩል ባሳየችው ቁርጠኝነት ስርጭቱን በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሰች ቢሆንም ዛሬም ቢሆን ማንኛውም ዜጋ መዘናጋት እንደሌለበት አሳስበዋል፡፡



አቶ ወንድሙ ኩመራ እና ወ/ሮ ማረፊያ ማሞ የኢንስቲትዩቱ ሴቶች ጉዳይ ኃላፊ ለበዓሉ የተዘጋጀውን ዳቦ የመቁረስ እና ሻማ የማብራት ስነስርዓት ያካሄዱ ሲሆን ባለፉት ዓመታት በኤድስ በሽታ ሕይወታቸውን ያጡ ዜጎችን ለማስታወስ ሠራተኞች የጧፍ ማብራት ሥነሥርዓት አድርገዋል፡፡